# የስንባ ነቀርሳ መቆጣጠሪያ መርሀ - ግብር (ፕሮግራም)

## ኢንፎርሜሽን ለወላጆች

---

### ልጅዎን ከሳንባ ነቀርሳ ስለመጠበቅ (ስለመከላከል)

---

**1 የስናባ ነቀርሳ ምንድን ነው?**

የሳንባ ነቀርሳ (ቲ.ቢ) (T.B) አብዛሀኛውን ጊዜ ሳንባን እና አንዳንድ ጊዜም ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን የሚያጠቃ ኃይለኛ በሽታ ነው። በ ሽታው ካለበት ሰው ሳንባ በሚሳል የሳል ኃይል በሚወረወሩ ተህዋሲያ ን (ጀርሞች) አማካይነት ወደ ጤነኛ ሰ ዎች ይተላለፋል፣ ይሰራጫል።

**2 እንዴት እራሴን ልጠብቅና ልከላከል እችላለሁ?**

ቢሲጂ (BCG) በላይኛው የግራ ክንድ ላይ በቆዳ ስር የምትወጋ ትንሽ የምርፌ ጠ ብታ ነች።ትናንሽ ሕጻናትን ከበጣም ኃይለኛውና ብርቱው የሳንባነቀርሳአይነት (ቲቢ) ለ መከላከል እጂግ በጣም ጥሩ ምድሀኒት ነች።

**3 ቢሲጅን (BCG) መውሰድ የሚገባው ማን ነው?**

ይህንን ክትባት ለመውሰድ መመዘኛውን የሚያማሉት በቁጥር ባጣም ጥቂት ሕጻናት ብቻ ናቸው። እንዲያው መደዳውን ለሁሉም ሕጻናት አይሰጥም።

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሳ በጣም አሳሳቢ የስንባ ነቀርሳ አደጋ ያንዣበበበ ት ሁኔታ ውስጥ ናቸው በሚያሰኝ አስጊ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ጨቅላ ሕጻናት ኖርማል ቢሲጂ ይሰጣል፣

አሳሳቢ ሁኔታን ያዘሉ ተብለው የሚገመቱት ሁኔታዎችም፣

- ሕጻኑ አንድም አሁን ትኩስ የሳንባ ነቀርሳ ያለበት፣ ወይም ከዚህ ቀደም የሳንባ ነቀርሳ የነበረበት ሰው ከሚኖርበት ቤት ወይም ቤተስብ/ሁዋናው (የቤተስብ ክልል) ውስጥ የሚኖር/የምትኖር ከሆነ
- አንደኛው ወይም ሁለቱም የሕጻኑ ወላጆች አመጣጣቸው ከሰላማዊው ደሴት (የፓ ሲፊክ ህዝቦች) ከሆኑ፣
- የሳንባ ነቀርሳ በከፍተኛ ሁኔታ በተደጋጋሚ በሚከሰትባቸው✷✷ ሀግሮች ውስጥ ባ ለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ለስድስት ወራትና ከዚያም በላይ ለሚሆን ጊዜ የቆየ ወላጅ ወይም የቤተስብ አባል ሕጻኑ ከሚኖርበት ቤት ውስጥ ካለ፣
- የሳንባ ነቀርሳ በከፍተኛ ሁኔታ በሚከሰትባቸው ሀግሮች በመጀመሪያዎቹ የአምስት ዓመታት ጊዜያቸው ውስጥ ለ 3 ወራት ወይም ከዚያ በላይ የሚኖሩ ከሆነ፣✷

*ሁሉም ሀገሮች፣ ከ አውስትራሊያ፣ አውስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ካናዳ፣ ቸክ ሪፑብሊክ፣ ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሆላንድ፣ አይስላንድ፣ አየርላንድ፣ እስራኤል፣ ጣሊያን፣ ሉግዘንበርግ፣ ማልታ፣ ሞናኮ፣ ኒው ዚላንድ፣ ኖርዌ፣ ስሎቫኪያ፣ ስዊድን፣ ስዊትዘርላንድ፣ ታላቋ ብሪታኒያ (ዩናይትድ ኪንግደም)፣ እና ዩኤስ አሜሪካ፣ በስተቀር።

**ይህ ምልከታ ፍጹማዊ አይደለም። አንድ ኅልማሳ የውጭ ተወላጅ ከሆነና የሳንባ ነቀርሳ በከፍተኛ ሁኔታ በሚከሰትባቸው ሀግሮች ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ ቢያንስ ለስድስት ወራት ያክል ቆይቶ ከሆነ ምንጊዜም ቢሆን ክትባቱን መውሰዱ ይመረጣል።

**4 ልጄ ቢሲጂ (BCG)ን እንዲወሰድ የሚመረጠው በጣም ጥሩው ጊዜ መቸ ነው?**

ልጅዎ ቢሲጂ (BCG)ን ቢወስድ የሚመረጠው ባጣም ጥሩው ጊዜ ሕጻኑ በተወለደ በጥቂት ቀናት ጊዜ ውስጥ ቢሆን ነው። ይህም እርሰዎ በሆስፒታል ውስጥ ወይም በኮሚዩኒቲ ክሊኒክ ውስጥ እንዳሉ ሊዘጋጅለዎት፣ ሊሰናዳለዎት ይችላል። ጉዳዩን በተመለከተም አዋላጅዎን ወይም የቤተስብ ሀኪመዎን ያነጋግሩ። የስምምነት ቅጽ (ፎርም) እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

**5 ቢሲጂ (BCG) ገንዘብ ያስወጣልን?**

የቢሲጂ ክትባቶች የመብት ማረጋገጫ ላላቸው ደንበኞች ነጻ ነው።

**6 ቢሲጂ (BCG) ከተወስደ በኃላ ምን ይሆናል?**

- ከአንድ እስከ ስድስት ሳምንታት ከሚሆን ጊዜ በኃላ መርፌው በተወጋበት ቦታ ላይ ትንሽ ቀይ ቁስለት ነገር ሊታይ ይችላል። ይህም ለመዳን የሚወስድበት ጊዜ ጥቂት ሳምንታት ብቻ ነው።
- መርፌው በተወጋበት ቦታ ላይ ትንሽ ጠባሳ ሊቀር ይችላል።
- እንዳንድ ጊዜ ቁስለቱ ለሁለት ወራት ያክል ሊያዥ (እንባ ነገር ሲያለቃቅስ) ሊቆይ ይችላል። ይህ ደግሞ ከክትባቱ በኋላ ሊከስት የሚችል ኖርማል ባህሪው ነው። የሚያዠውን ቁስልም በደረቅ ማሸጊያ (በሚያጣብቅ ፕላስተር ሳይሆን በጎዝ፣ (የህክምና ጥጥ)) መሸፈን በጣም ጥሩ ነው።

**7 የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ የህዝብ ጤና አገልግሎት ነርስን ማግኘት ያስፈልገዎታል።**

- ከባቱ ከተደረገበት ቦታ ላይ መግል የቋጠሩ እባጭ ነገሮች ከታዩ፣
- ከትባቱ ከተሰጠ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ውስጥ ቁስለት ከታየ፣
- ከቁስሉ የሚያለቃቅሰው እዥ ባለበት ሁኔታ ከሁለት ወራት በላይ ከቀጠለ፣

**8 ተጨማሪ መረጃ (ኢንፎርሜሽን) ከፈለጉ ቀጥሎ የተመለከተውን አድራሻ ይጠቀሙ፣**

*ስም---------------------------------------------ኃላፊነት-----------------------------------------*

*ስልክ: 262 1855*

መልካም ጊዜ-------------